5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት



1. **ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- ዴሞክራሲንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምንነትን በደረጃቸው ይገነዘባሉ።
- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸውን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያውቃሉ።
- የልዩነት ምንነትንና ልዩነትን እንዴት አቻችሎ መኖር እንደሚቻል ይረዳሉ፣
- የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ምንነት ይገነዘባሉ።
- የውጭ ግንኙነት ምንነትን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የዴሞክራሲን ትርጉም በምሳሌ ይገልፃሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮች የሚገለጹባቸውን መንገዶች ይለያሉ፣ | 1.1 ዴሞክራሲ ምንድን ነው? (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.1.1 ትርጉም/ቀለል ያለና አጭር ማብራሪያ/፣<br>1.1.2 የዴሞክራሲ ምንነት፤ በትምህርት ቤት የሚገለጽባቸው መንገዶች፣ | • የዴሞክራሲ ሥርዓትን ተማሪዎች በአግባቡ እንዲረዱት ለማስቻል ዴሞክራሲን አስመልክቶ አንድ ጉዳይ (Case study) ማቅረብና ተማሪዎች በቡድን ተከፍለው እንዲወያዩበት ማድረግ። የተወያዩበትን ጉዳይ ከትምህርት ቤታቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያዛምዱና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ እንዲያስረዱ ማድረግ።<br>• ከዴሞክራሲ ሥርዓት አንፃር በትምህርት ቤታቸው ሊሻሻሉ የሚገቡ አሠራሮችንም እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ ከዚያም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለምን እንደሚያስፈልግ መምህሩ የማጠናከሪያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ማጠናቀቅ።<br>• በተጨማሪም ተማሪዎች በዴሞክራሲ አሰራር ላይ ግልጽና ተጨባጭ እውቀትና ግንዛቤ እንዳያዳብሩ ለመርዳት በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኙ ልዩ ልዩ ተቋማትን ለምሳሌ፣ የፖሊስ፣ የፍርድ ቤቶች፣ የቀበሌ ጽ/ቤትን እንዲጎበኙ ማድረግ። |
| • የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን ምንነት ይገልፃሉ፣<br>• የጓደኞቻቸውን መብቶች | 1.2 የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ምንነት (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.2.1 የሰብዓዊ መብቶች ምንነት፣ | • ቀደም ባለው ትምህርት ተማሪዎቹ ስለዴሞክራሲ የተወያዩባቸውን ነጥቦች እራሳቸው አስታውሰው በራሳቸው አገላለጽ ትምህርቱን እንዲከልሱ ማድረግ። በማስከተልም ሰብዓዊ መብቶች ሰዎች ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ ያሉዋቸው መብቶች መሆናቸውን ለማስረዳት እንዲያስችል አንድ ጉዳይ (Case study) በማቅረብ ተማሪዎቹ ስለሰብዓዊ መብቶች ምንነት |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ያከብራሉ፣<br>• የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይገልፃሉ፣ | 1.2.2 የዴሞክራሲ መብቶች ምንነት፣ | ላይ በቡድን ተወያይተው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• በሚቀጥለው የክፍል ደረጃ የሚማሩት ቢሆንም አጠር ባለመልኩ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት እንዲገነዘቡ በማድረግ ትምህርቱን ማጠናቀቅ፣ |
| • በክፍልና በትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ይዘረዝራሉ፣<br>• በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ መኖር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• ልዩነቶቻቸውን አቻችለው አብረው ይጫወታሉ፣ | 1.3 ልዩነት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.3.1 በክፍልና በት/ቤት ውስጥ በተማሪዎች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች፣<br>1.3.2 ልዩነትን አቻችሎ በሰላም መኖር፣<br>- ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ የመኖር ምንነት፣<br>- ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ የመኖር ጠቀሜታ | • ተማሪዎቹን በቡድን (በሦስት ወይም በአራት) በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን አባላቱን አስመልክቶ በውስጡ የያዛቸውን ልዩነቶች (በመልክ፣ በቀለም፣ በቁመት፣ በውፍረት፣ በብሔር፣ ወዘተ) እና እነዚህ ልዩነቶች እንዲኖሩ ያደረገው ምን እንደሆነ እንዲያቀርቡ ማድረግ። እነዚህን ልዩነቶች እንዳይኖሩ ማድረግ ይቻል ወይም አይቻል እንደሆነም ተማሪዎች እንዲወያዩበት በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ።<br>• ሰዎች ደግሞ በተፈጥሮ የተለያዩ ከሆኑ ለነገሮች የራሳቸው አስተሳሰብ፣ የራሳቸው አመለካከት፣ አረዳድ ወዘተ አላቸው ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አብሮ በመኖር ሒደት ውስጥ የኔ ትክክል ነው የከሌ ስህተት ነው ማለት አይቻልም። እንዲህ ካልን ወደ ግጭት እናመራለን። ይህ ግጭት እንዳይከሰትና በልዩነቶቻችን ውስጥ በሰላም አብሮ ለመኖር እንዲቻል እነሱ ከጓደኞቻቸው፣ ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ዓባላት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው እንዲሁም ልዩነቶቻቸውን አቻችለው መኖራቸው የሚሰጠውን ጥቅም በቡድናቸው ተወያይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• ልዩነቶቻቸውን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የተሳናቸው የአንድ መንደር ነዋሪዎች ባነሱት ግጭት የደረሰ ጉዳትን የሚያትት ልቦለድ ጽሑፍ በማዘጋጀት ወይም የተዘጋጀ በማቅረብ ለተማሪዎች ማንበብና ከልቦለድ ጽሑፉ የተገነዘቡትንና የጉዳዩ ባለቤት ቢሆኑ ኖሮ ችግሩን እንዴት ሊያስወግዱ ይችሉ እንደነበር እንዲወያዩበት ማድረግ። |
| • የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራሉ።<br>• የክልል መንግሥታት ምንነትን ያስረዳሉ<br>• የከተማ አስተዳደር | 1.4 የመንግሥት ሥርዓት በኢትዮጵያ፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.4.1 የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ምንነትና አስፈላጊነት፣ | • እነሱ የሚኖሩበት ክልል እራሱን ማስተዳደር በመቻል ተገኝቷል የሚሏቸውን ጥቅሞች ከወላጆቻቸውም ሆነ ወይም ከሌላ ሰው በመጠየቅ ክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ባቸው ማድረግና የክልላቸውን መንግሥት ዴሞክራ ሲያዊነት በተመለከተ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲ ሰጡ ማድረግ። ክልላዊ መንግሥታት ለዜጎች ያጐናፀፏቸው መብች የዴሞክራሲ ውጤት መሆኑና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የዜጐችን መብቶችና ጥቅሞች ማስከበሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን መገንዘባቸውን በማረጋገጥ ትምህርቱን ማጠናቀቅ፣ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ምንነትን ይገልፃሉ፣ | - የዜጐችን መብትና ጥቅሞችን በሕጋዊ አኳኋን ለማስጠበቅ፣<br>1.4.2 የፌዴራል መንግሥት ምንነት፣<br>1.4.3 የክልል መንግሥታት ምንነት፣<br>1.4.4 የከተማ አስተዳደር ምንነት፡ | |
| | | • የመማሪያ ክፍላቸውን የፌዴራል ሥርዓት ተምሳሌት ማድረግ። እነሱ በሚማሩበት ክፍል ተማሪዎች በረድፍ ተከፍለው ነው የሚማሩት። አጠቃላይ ደግሞ ክፍሉ እራሱን ችሎ አለ። ተማሪዎቹ በአንድ በኩል የረድፉ አባል ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የክፍላቸውም አባላት ናቸው። ለምን የመማሪያ ክፍልን በረድፎች መከፋፈል እንዳስፈለገ ቀደም ሲል በተመሠረቱ ቡድኖች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲወያዩና እንዲያስረዱ ማድረግ። ይህንኑ ጉዳይ በማነፃፀር የተለያዩ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሏት ኢትዮጵያን ከአንድ ማዕከል ከማስተዳደር ይልቅ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸው መግለጫ ስላላቸው እራሳቸውን እንዲያስተዳድሩና በጋራ ጉዳዮች ላይ ደግሞ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ተማሪዎቹ እንዲወያዩበት በማድረግ የፌዴራል መንግሥትን ምንነትና አስፈላጊነትን በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የውጭ ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምንነትን ያስረዳሉ፣<br>• የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለምን እንደሚያስፈልግ በሁለት ምሣሌዎች | 1.5 የውጪ ግንኙነት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.5.1 የውጪ ግንኙነት ምንነትና ፣ የውጪ ግንኙነት፣ ፖሊሲ | • ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር በሰላም አብሮ ለመኖርና በሥራቸውም ውጤታማ ለመሆን ምን እንደሚያስፈ ልጋቸው እንዲወያዩበት ማድረግ። ውይይታቸው ሊያጠነጥን የሚገባው አንድ የሚመሩ በት መርህ መኖር ዙሪያ ሊሆን ይገባዋል። ለምሳሌ ከቤተሰቦቻ ቸው ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር የቤተሰቡን አባላት ማክበር፣ ቤተሰቡን አቅም በፈቀደ መርዳት፣ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይገልፃሉ፣ | | |
| | | (የበሉበትን ዕቃ ማጠብ፣ የተኙበትን አልጋ ማንጠፍ፣ ሌሎች የቤት ውስጥ ሥራዎችን ማገዝ ወዘተ) ያስፈልጋል። ከጓደኞቻቸውም ጋር አብሮ ለመኖር ጓደኛን ማክበር፣ የሚናገረውን ማዳመጥ፣ ያልተግባቡባቸውን ጉዳዮች በጥሞና ማስረዳት ባጠቃላይ ሥነምግባር የተላበሰ ሰው መሆንን ይጥይቃል። እነዚህ ነጥቦች የለት ተለት መመሪያዎች ሊሆኑ ይገባል። እንደዚሁም አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ባላት ግንኙነት የምትመራበት መመሪያ ወይም ፖሊሲ ያስፈልጋታል፣ እነዚህን ነጥቦች መሠረት አድርገው ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግና በፖሊሲ አስፈላጊነት ላይ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>• የተማሪዎቹን ግንዛቤ ለማዳበር እንዲያስችልም ሳይን ዛዛ የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ከሌሎች ሀገራት ጋር በመከባበርና የጋራ ጥቅምን በማራመድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን በአጭሩ መግለጽ። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ መካከል የሚታየውን የውጤት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዴሞክራሲን ትርጉም በምሳሌ ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮች የሚገለጹባቸውን መንገዶች ይለያሉ፣፣ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮች የሚገለጹባቸውን መንገዶች ይለያሉየሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን ምንነት ይገልፃሉ፣ የጓደኞቻቸውን መብቶች ያከብራሉ፣ የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይገልፃሉ፣በክፍልና በትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ መኖር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣ልዩነቶቻቸውን አቻችለው አብረው ይጫወታሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራሉ።የክልል መንግሥታት ምንነትን ያስረዳሉ የከተማ አስተዳደር ምንነትን ይገልፃሉ፣ የውጭ ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምንነትን ያስረዳሉ፣የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለምን እንደሚያስፈልግ በሁለት ምሣሌዎች ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዴሞክራሲን ትርጉም በተግባር ያሳያሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችን ይተገብራሉ ፣የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን ያከብራሉ፣ የጓደኞቻቸውን መብቶች ያከብራሉ፣ የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶችን አንድነትና ልዩነትን በተግባር ያሳያሉ፣በክፍልና በትምህርት ቤት ውስጥ

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

በተማሪዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ያከብራሉ ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው ልዩነቶችን አቻችለው በሰላም አብረው ይኖራሉ ፣፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ዋና ዋና ተግባራት ያስረዳሉ። ፣ የውጭ ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ ምሳሌ በመስጠት ይገልፃሉ፣የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምንነትን ያስረዳሉ፣የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለምን እንደሚያስፈልግ በምሣሌዎች ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

# 5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

## 2. የሕግ የበላይነት

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የሕገመንግሥትና የሌሎች ሕጐችን ምንነትና ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- የሕግ የበላይነት ለምን እንደሚያስፈልጉ ይረዳሉ።
- የትምህርት ቤት ሕጎችና ደንቦች ለምን እንደሚያስፈልጉ ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥቶች ምን እንደሆኑ ለይተው ይገልፃሉ፣<br>• የሌሎች ሕጐችንና ደንቦችንአስፈላጊነት ያስረዳሉ፣<br>• የትምህርት ቤት ደንቦች ለምን እንደሚያስፈልጉ ይገልፃሉ፣<br>• የትምህርት ቤት ደንቦች ከሕገመንግሥትና ከሌሎች ሕጎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያስረዳሉ፣<br>• በትምህርት ቤታችውና በአካባቢያችው ሕግና ደንብን ያከብራሉ፣ | 2.1 ሕገመንግሥት ምንድን ነው (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.1.1 የሕገመንግሥት አስፈላጊነት<br>2.1.2 የክልል ሕገ መንግሥታት<br>2.1.3 ሌሎች ሕጐችና ደንቦች፣<br>2.1.4 የት/ቤት ደንቦች<br>- ሥርዓት ያለው የመማር ማስተማር ሒደት እንዲኖር፣<br>- በተማሪዎች መካከል እኩልነትን ለማስፈን፣<br>- የትምህርት ቤት አመራርንና አሠራርን ለመቆጣጠር፣ | • ሕገመንግሥት ምን ዳንደሆነ ለማስረዳት እንዲያስችል ተማሪዎች አሥር የሚያክሉ ተወካዮቻቸውን በመምረጥ አንድ ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ ማድረግ። ይህ ኮሚቴ በመምህሩ እየተረዳ ለክፍላቸው መተዳደሪያ የሚሆን ሕግ እንዲያዘጋጅ ማድረግ። ኮሚቴው ያዘጋጀውን ሕግ ለክፍሉ በማቅረብ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ። በተሰጠ አስተያየት መሠረት ሕጉን ማሻሻልና በተማሪዎች እንዲፀድቅ ማድረግ። ይህ ሕገ ከፀደቀ በኋላም ኮሚቴው የመተዳደሪያ ሕግ ሆኗል ብሎ እንዲያውጅ ማድረግ፣<br>• ይህ ሕግ በእንዲህ ዓይነት ተዘጋጅቶና ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ ክፍሉን በተመለከተ ምን ዓይነት ሕግ እንደሆነና ማን ሊሽረው እንደሚችል ወይም እንደማይችል ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩበት ማድረግ፣ በውይይታቸውም ሕጉ ክፍሉን በተመለከተ የበላይ ሕግ እንደሆነና ከአጠቃላዬ ተማሪ በመለስ ማንም ሊሽረው እንደ ማይችል በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ በዚሁ መሠረት ሕገመንግሥት የሚዘጋጅ መሆኑንና ከሌሎችም ሕጐች የሚለይበትን ባህሪያት እንዲረዱ ማድረግ፣ |
| • የሕግ የበላይነትን ምንነትን ያስረዳሉ፣<br>• ለሕግ የበላይነት መገዛት ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፣ | 2.2 ለሕግ የበላይነት መገዛት (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.2.1 ለሕግ የበላይነት መገዛት | • ቀደም ባለው ክፍለ ትምህርት ተማሪዎቹ ለክፍላቸው ደንብ (ሕግ) አውጥተዋል፣ ያ ያወጡት ሕግ በማንም ተማሪ ላይ ልዩነት ሳያደርግ (ሁሉንም በእኩል ዐይን በማየት) በሁሉም ላይ ተፈፃሚ እንደሆነና ማንም ሰው (ከራሳቸው ከተማሪዎቹ በስተቀር) ሊሽረው |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የዜጐች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆን ምንነትን ያስረዳሉ፣ | መንነት?<br>2.2.2 ለሕግ የበላይነት መገዛት ለምን ያስፈልጋል?<br>2.2.3 የዜጐች በሕግ ፊት እኩል መሆን ምንነት፣ | እንደማይችል መግባባት ላይ ተደርሷል።<br>• ቀደም ሲል ካደረጉት ውይይት በመነሳት የሕግ የበላይነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ለሕግ የበላይነት መገዛት ለምን እንደሚያስፈልግና የዜጐች በሕግ ፊት እኩል መሆን ምን ማለት እንደሆነ በሦስት ቡድኖች ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማዳረግ። የቡድን ውይይታቸውንም ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግና በሦስቱም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መላውተማሪ አስተያየት እንዲሰጥበትና የጋራ መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ማድረግ። |
| • በተማሪነታቸው የሚጠበቅባቸውን ሥነምግባር ያክብራሉ፣<br>• እናትና አባትን ማክበር ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፣<br>• እናት፣ አባትንና ታላቆቻቸውን ያከብራሉ፣ | 2.3 ሥነምግባር፣ (1 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.3.1 ሥነምግባር ምንድን ነው?<br>- እናት አባትን ማክበር፣<br>- ታላቅን ማክበር፣<br>- የግል ንጽሕናን መጠበቅ፣ | • የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ተማሪዎች እንዲማሩ ካስፈለገበት ምክንያት ውስጥ አንዱና ዋንኛው ተማሪዎች በሥነምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው። ወጣቶቹ ጥሩ ዜጐች እንዲሆኑ ከነሱ የሚጠበቅ ሥነምግባር አለ። የክፍሉን ተማሪዎች በሁለት ቡድን በመክፈል በነሱ ደረጃ ምን ዓይነት ሥነምግባር እንደሚጠበቅ እንዲገለፁና የራሳቸው ደምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ውይይታቸውን በይዘቶቹ ላይ በተዘረዘረት ጉዳዮች ዙሪያ እንዲያጠነጥን ከመምህሩ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቃል፣ |
| • የሥልጣን ምንነትንና የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣<br>• የክፍል አለቃ ሲሆኑ ሥልጣናቸውን በሕጉ መሠረት ይጠቀማሉ፣ | 2.4 ሥልጣን (1 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.4.1 የሥልጣን ምንነት፣<br>2.4.2 የሥልጣን ገደብ ምንነትና ጠቀሜታ<br>2.4.3 በክፍል አለቃና በት/ቤት መሪዎች ላይ የሥልጣን ገደብ መደረጉ ለምን ይጠቅማል ? | • በቤተሰብ ውስጥ አባትና እናት ልጆቻቸውን ይበጃል ባሉት መንገድ የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው፣ ርዕሳነ መምህራን ትምህርት ቤትን በበላይነት የማስተዳደር መብት አላቸው፣ የክፍል አለቆች የክፍሉን ፀጥታና አንዳንድ አስተዳደሪያዊ ሥራዎችን የማከናወን ሥልጣን አላቸው። ይሁን እንጂ ይህ ሥልጣናቸው በሕግ የተገደበና የፈለጉትን ሁሉ ማድረግ የሚያስችላቸው አይደለም። የፈለጉትን ማድረግ የሚያስች ላቸው ከሆነ ሕገወጥነት ይሰፍናል። ተማሪዎች ይህን እውነታ ከተገነዘቡ ዘንዳ በቡድን እንዲከፋፈሉ በማድረግ ሥልጣንና የሥልጣን ገደብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዲሁም የሥልጣን ገደብ ማስቀመጡ ለምን እንደሚጠቅም ለምሳሌ በክፍል አለቃ ላይ የሥልጣን ገደብ ባይኖር ምን ሊከሰት እንደሚችል እንዲወያዩበትና የጋራ መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |
| • የሚስጥርን ምንነት ይገልፃሉ፣<br>• የግል ሚስጥር ባህሪን | 2.5 ሚስጥር (1 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.5.1 የግል ሚስጥር | • ሚስጥር ምን እንደሆነ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስረዳ ማድረግ። በማስከተልም የግል ሚስጥር ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁት ይገባል ወይስ ለራስ ብቻ የሚያዝ ጉዳይ ነው በሚል |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይዘረዝራሉ፡<br>• ሚስጥር መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፣ | | ተማሪዎች እንዲወያዩና የራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሙስናን ምንነት ያስረዳሉ፣<br>• የሙስና ተግባራት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ሙስና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣ | 2.6 ሙስና (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.6.1 ሙስና ምንድን ነው?<br>2.6.2 በትም/ቤትና በመኖሪያ አካባቢ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ተግባራት መገለጫዎች፣<br>2.6.3 ሙስና የሚያስከትለው ጉዳት | • ሙስና አንድ ለራስ የማይገባ ጥቅምን ለማግኘት ወይም ሌላ ሰው የማይገባውን ጥቅም እንዲያገኝ በማሰብ ጉቦ መስጠት ወይም መቀበል፣ በዘመድ አዝማድ መሥራት፣ የራስ ባልሆነና የመንግሥትና የሕዝብ በሆነ ሀብት መገልገል ወዘተ ነው።<br>• ተማሪዎች ስለሙስና የራሳቸው የሆነ አገላለጽ ይኖራቸው እንደሆነ ተራ በመስጠት እንዲገልጹ ማድረግ። የሙስና ትርጉምን በሚገባ መጨበጣቸው ከተረጋገጠ በትምህርት ቤታቸውና በመኖሪያ አካባቢያቸው የሙስና መገለጫዎችን እንዲያቀርቡ ማዳረግና በዚሁ የሙስና መገለጫዎችና አስከፊነትን አስመልክቶ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥቶች ምን እንደሆኑ ለይተው ይገልፃሉ፣የሌሎች ሕጎችንና ደንቦችንአስፈላጊነት ያስረዳሉ፣የትምህርት ቤት ደንቦች ለምን እንደሚያስፈልጉ ይገልፃሉ፣የትምህርት ቤት ደንቦች ከሕገመንግሥትና ከሌሎችሕጎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያስረዳሉ፣የሕግ የበላይነትን ምንነትን ያስረዳሉ፣ ለሕግ የበላይነት መገዛት ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፣የዜጐች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆን ምንነትን ያስረዳሉ፣በተማሪነታቸው የሚጠበቅባቸውን ሥነምግባር ያከብራሉ፣እናትና አባትን ማክበር ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፣እናት፣ አባትንና ታላቆቻቸውን ያከብራ የሚስጥርን ምንነት ይገልፃሉ፣የግል ሚስጥር ባህሪን ይዘረዝራሉ፡ ሚስጥር መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፣የሙስናን ምንነት ያስረዳሉ፣የሙስና ተግባራት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣ ሙስና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣ በትምህርት ቤታችውና በአካባቢያችው ሕግና ደንብን ያከብራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥቶች ምን እንደሆኑ ለይተው ይገልፃሉ፣የሌሎች ሕጎችንና ደንቦችንአስፈላጊነት ያስረዳሉ፣የትምህርት ቤት ደንቦች በማክበር አርአያ ይሆናሉ፣የትምህርት ቤት ደንቦች ከሕገመንግሥትና ከሌሎችሕጎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በምሳሌ ይገልፃሉ፣የሕግ የበላይነትን ያከብራሉ፣

## 5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

፣ዜጐች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል በተግባር ያሳያሉ፣በተማሪነታቸው የሚጠበቅባቸውን ሥነምግባር ያክብራሉ፣እናትና አባትን በማክበር አርአያ ይሆናሉ፣ የሚስጥርን ይጠብቃሉ፣ ፣ሙስናን የታገላሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

3. **እኩልነት**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- የእኩልነት ምንነትን ያውቃሉ።
- ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሀገሪቱ ውስጥ ያሏቸውን መብቶች ያውቃሉ።
- የዜጐች፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ዋና ዋና የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ይረዳሉ።
- የአካል ጉዳተኝነት ምንነትን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የእኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ<br>• የኢትዮጵያ ብሔር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች የእኩልነት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 3.1 የእኩልነት ምንነት፣<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>3.2 የብሔር ብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች፣<br>3.2.1 ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣<br>3.2.2 በራስ ቋንቋ የመገልገል መብት፣<br>3.2.4 እኩል የትምህርት እድል የማግኘት መበት፣<br>3.2.5 እኩል የሥራ እድል የማግኘት መበት፣ | • በመጀመሪያ እያንዳንዱ ተማሪ እኩልነት ሲባል ምን እንደሚረዳ እንዲገልፅ ማድረግ። በማስከተልም ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን ማስረዳት። እነዚህ ብሔሮች ብሔረሰቦች የሕዝቦች እያንዳንዳቸው የራሳቸው ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች ያሉዋቸው መሆኑን መግለጽ፣ ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸው ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እንዳሏቸው ተማሪዎቹ እራሳቸው በአካባቢያቸው የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችን እየጠቀሱ በምሳሌ እንዲያስረዱ ማድረግ። እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦች በአሁኑ ጊዜ የሚኖሩበትን ክልል ራሳቸው እያስተዳደሩ መሆናቸውን አስገንዝቦ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደራቸው የሚሰጠውን ጥቅም ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ።<br>• የቡድን ውይይቱን ውጤት ለአጠቃላይ ክፍል በማቅረብ ተማሪው ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እራሳቸውን ማስተዳደራቸው የሚሰጠውን ጠቀሜታና ይህም የእኩልነት መገለጫ መሆኑን ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• በዚህ የእድሜ ደረጃ እኩል የትምህርትና የሥራ እድል ሲባል ተማሪዎች አንድ ዓይነት ትምህርትና አንድ ዓይነት ሥራ ሊመስላቸው ይችላል። ስለዚህ ይህ አለመሆኑን ለማስረዳት እንዲቻል ተማሪዎቹ እኩል የትምህርት እድልና እኩል የሥራ ዕድል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እራሳቸው እንዲገልፁና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። የሰጡት ድምዳሜ ስሕተት ሆኖ ከተገኘ በመምህሩ ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ማጠናቀቅ። |
| • የእኩል ተጠቃሚነት መብት | 3.3 የእኩልነት መብት በትምህርት | • ተማሪዎቹን በትምህርት ቤት የእኩልነት መብት እንዳለና እንደሌለ መጠየቅ። አለ ካሉ |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያብራራሉ፣ | ቤት (2 ክፍለ ጊዜ)<br>3.3.1 የእኩል ተጠቃሚነት መብት፣ | መገለጫዎቹ ምን እንደሆኑ እንዲዘረዝሩ ማበረታታት። መልሳቸው የለም ከሆነ ደግሞ እንዴት እንደሚገለጡና ለወደፊቱ ምን ሊደረግ እንደሚገባው እንዲያስረዱ በማድረግ በትምህርት ቤት የእኩል ተጠቃሚነት መብትን አስመልክቶ የራሳቸውን መደምደሚያ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የፆታ እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• በትምህርት ቤታ ቸው የሚታዩ የሴቶ ችና የወንዶች ተማሪ ዎች የእኩልነት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው የወንዶችና የሴቶች እኩልነት መረጋገጥ ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣ | 3.4 የፆታ እኩልነት፣<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>3.4.1 የሴቶችና የወንዶች እኩልነት በሁሉም ዘርፍ፣<br>3.4.2 በትምህርት ቤት የሴትና የወንድ ተማሪዎች የእኩል መብት መገለጫዎች | • በመጀመሪያ ደረጃ ፆታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹ እንዲገልፁ ማድረግ። ከዚያም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል በወንድና በሴት መካከል አሉ የሚሉትን ልዩነቶች አስመልክቶ እንዲወያዩና ልዩነቶቹን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። ይህን የቡድን ውይይት ክፍል ውስጥ በሚያመጡበት ጊዜ ውይይቱ ወንድ ሊሰራ የሚችለው ሴት ግን ልትሰራ የማትችለውን ሥራ ትኩረት ሰጥተው እንዲወያዩበት ማድረግ።<br>ለዚህም እንዲረዳ በቤታቸው ውስጥ ከእናትና ከአባት፤ ከወንድምና ከእህት የበለጠ የቤት ውስጥ ሥራ የሚሠራው ማን እንደሆነ እንዲያጤኑት ማድረግ። ይህም ውይይት የተፈጥሮ ልዩነት ካልኖረ በስተቀር በሴትና በወንድ መካከል ልዩነት የለም ወደሚል ድምዳሜ እንዲያደርሳቸው ውይይቱን መምራት ተገቢ ይሆናል።<br>• በወንድና በሴት መካከል ልዩነት ከሌለ ደግሞ ይህ የእኩልነት መብት በትምህርት ቤታቸው እንዴት እንደሚገለጥ በቡድንና በክፍል ውይይታቸው አካተው እንዲነጋገሩበትና መታረም ይገባዋል የሚሉት ነገር ካለ ሃሣብ እንዲሰጡበት በማድረግ የጋራ አቋም እንዲይዙ ማድረግ። |
| • የባህል እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የባህል እኩልነት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣ | 3.5 የባህል እኩልነት<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>3.5.1 የባህል እኩልነት ምንነት፣<br>3.5.2 ባህልን የማዳበር አስፈላጊነት፣ | • ተማሪዎቹ ቀደም ባለው ክፍለ ጊዜ ስለ ቋንቋና ሃይማኖት በመጠኑም ቢሆን ተምረዋል፣ እዚህ ጋ የሚያስፈልገው ያንን ትምህርት ማጠናከር ነው። ስለሆነም የባህል መገለጫዎች የሆኑትን ተማሪዎች እንዲዘረዝሯቸው ማድረግ።<br>• አንድ ሕዝብ ባህሉን ማዳበሩ የራሱን ማንነት ከማበልፀጉም በላይ ለሀገር እድገትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ከዚህም በላይ ማንም ሕዝብ ባህሉን ማዳበሩ ሕገመንግሥታዊ መብቱ ነው፣ ስለሆነም ተማሪዎቹ ባህልን የማዳበር አስላጊነት ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ውይይታቸው ከላይ ወደ ተጠቀሰው ነጥብ እንዲያመራና የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ። |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | |
| • የአካል ጉዳተኝነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• የአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ካገኙ ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደ ርጉ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣ | 3.6 የአካል ጉዳተኝነት፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>3.6.1 የአካል ጉዳተኝነት ምንነት፣<br>3.6.2 የአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጓቸው ድጋፎች፣ | • የአካል ጉዳተኝነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ። ተማሪዎቹ ሊሰሩት የሚችሉት፤ የአካል ጉዳተኞች የተባሉት ሊሰሩት የማይችሉት ነገር ምን እንደሆነ ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ። ለምሳሌ ተማሪዎቹ ማየት የተሳናቸውን ወስደው እነሱ በወረቀት ላይ አይተው መፃፍ አይችሉም እኔ/እኛ ግን እንችላለን ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ማየት የተሳናቸው የብሬል አቅርቦት ካላቸው እነሱም እንደነሱ ጽፎ መማር እንደሚችሉ ማስገንዘብ ይቻላል።<br>• ውይይቱን በእንደዚህ ዓይነት በማስፋት የአካል ጉዳተኞች ከአካላቸው የተወሰነው ክፍል ባይሰራም ለዚያ ማካካሻ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ ካገኙ እንደማንኛውም ሰው ማንኛውንም ሥራ መሥራት እንደሚችሉ ተማሪዎቹ ተወያይተው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሃይማኖት እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ | 3.7 የሃይማኖት እኩልነት መብት ምንነት፣ | • ስለ ሃይማኖት መግለጫ መስጠት፣ በማስከተልም በአካባቢያቸው የሚመለኩትን ሃይማኖቶች እንዲገልፁ ማድረግ። በኢትዮጵያ የሃይማኖት እኩልነት የተረጋገጠ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በየተራ እንዲገልፁ በማድረግ ትምህርቱን ማጠናቀቅ፣ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፆታ እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ፣ በትምህርት ቤታ ቸው የሚታዩ የሴቶ ችና የወንዶች ተማሪ ዎች የእኩልነት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸው የወንዶችና የሴቶች እኩልነት መረጋገጥ ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣የባህል እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ፣

የባህል እኩልነት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣የአካል ጉዳተኝነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣የአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ካገኙ ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደ ርጉ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣የሃይማኖት እኩልነት ምንነትን ይገልፃሉ

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፆታ እኩልነትን ያከብራሉ፣ ፣፣የባህል እኩልነት ያከብራሉ፣፣ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፣የሃይማኖት እኩልነትን ያከብራሉ

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 4. ፍትሐዊነት

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የፍትሐዊነት ምንነትን ይረዳሉ።
- ፍትሕ ሊጣስ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ያውቃሉ፣
- የአድሎአዊ አሠራሮችን ምንነትና መገለጫዎቻቸውን ይረዳሉ።
- የማህበራዊ ተቋማትን ምንነትና አስፈላጊነትን ይገነዘባሉ።
- የፍትሐዊ አሰራሮች መኖር ለአካባቢያቸው ሰላም መስፈን አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባሉ።
- የግብር ምንነትን ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የፍትህ ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የፍትህ አስፈላጊነትን ይተነትናሉ፣<br>• ከጓደኞቻቸው ጋር ፍትሐዊ የሆኑ ግንኙነትን ይፈጥራሉ፡ | 4.1 ፍትህ፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>4.1.1 የፍትህ ምንነት፣<br>4.1.2 የፍትህ አስፈላጊነት፣<br>- እኩልነት ለማስፈን፣<br>- ሰላምን ለማረጋገጥ፣<br>- ማህበራዊ እድገትን ለማፋጠን፣ | • ተማሪዎቹን በየተራ በመጋበዝ ፍትህ ማለት ምን እንደሆነ እንዲገልፁ ማድረግ። የአገላለጽ ስሕተት ካለ በመጀመሪያ እራሳቸው እርስ በርስ እንዲተራረሙ ማድረግና ትክክለኛ ትርጉም ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• በማስከተልም ተማሪዎችን በሁለት ቡድኖች በመክፈል አንደኛውን ቡድን በት/ቤት ውስጥ በሚታዩ አድሎአዊ አሠራሮችና በሚያስከትሉት ውጤቶች ላይ፣ ሁለተኛውን ቡድን ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ በሚታዩ አድሎአዊ አሠራሮችና በሚያስከትሉት ውጤቶች ላይ ሪፖርት እንዲያቀርቡና ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ።<br>• ሁለቱም ቡድኖች የተወያዩባቸውን ነጥቦች ለክፍል አጠቃላይ ውይይት ማቅረብና ፍትህዊ አሠራር ከሌለ ሰላምንም ማስፈን ሆነ ማህበራዊ እድገትን ማረጋገጥ እንደማይቻል የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማስቻል። |
| • የአካባቢ የፍትሕ አካላትንና ተግባራቸውን ይተነትናሉ፣ | 4.2 የፍትህ አሰጣጥ ሂደቶችና በአካባቢያቸው የሚገኙ የፍትህ አካላት፣(2ክፍለ ጊዜ)<br>4.2.1 የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት በማሕበረሰብ ደረጃ<br>4. 2.2 የፍትሕ አካላት | • ተማሪዎቹን በሦስት ቡድን በመክፈል ቀበሌ፣ ፖሊስ ጣቢያና ፍርድ ቤት ተግባራቸው ምን እንደሆነ እንዲወያዩ ማድረግ። ቡድኖቹ የተወያዩባቸውን ጉዳዮች በክፍል ውስጥ በየተራ በማቅረብ ሁሉም ተማሪዎች አስተያየት በመስጠት እንዲሳተፉ ማድረግ።አጠቃላይ ውይይቱ እኒህ በአካባቢያቸው የሚገኙ ተቋማት የፍትህ ማስከበሪያ መሣሪያዎች እንደሆኑ ተማሪዎቹን ወደ ድምዳሜ የሚያደርስ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። |
| • ፍትህ ሊጣሱ የሚችሉባቸውን | 4.3 ፍትህ ሊጣሱ የሚችሉባቸው | • የፍትህን ምንነት ቀደም ባለው ክፍለ ጊዜ ተምረው አጠናቀዋል። ፍትህ ብለው |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| መንገዶች ይዘረዝራሉ፣<br>• በትምህርት ቤት ውስጥ አዱሎአዊ አሠራሮች የሚገለፁባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣<br>• በቀበሌ ደረጃ አድሎአዊ አሠራሮች የሚገለፁባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣ | ሁኔታዎች፣(2ክፍለጊዜ)<br>4.3.1 ሕግን አለማክበር፣<br>4.3.2 አድሎአዊ አሠራር መፈፀም፣<br>- አድሎአዊ አሠራ ሮች በት/ቤት፣<br>- አድሎአዊ አሠራሮች በቀበሌ፣<br>4.3.3 አድሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች፣ | ተማሪዎች የተረዱት ነገር በተለያዩ ሁኔታዎች ሊገሱ ይችላሉ። ፍትህ ከሚጣሱባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች ውስጥ ሕግን መጣስና አድሎአዊ አሠራሮችን መፈፀም ነው። ተማሪዎች ፍትህ የሚጣሱባቸ ውን ጉዳዮች እንዲረዱ ለማድረግ ክፍሉን በሁለት ቡድን መክፈል፣ ለአንደኛው ቡድን አዱሎአዊ አሠራር በትምህርት ቤት እንዴት እንደሚፈፀምና ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እንዲወያይ ማድረግ።<br>• ሁለተኛውን ቡድን ደግሞ አድሎአዊ አሠራር በቀበሌ ደረጃ እንዴት እንደሚፈፀምና ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እንዲወያይ ማድረግ። ሁለቱም ቡድኖች የውይይታቸውን ጭብጥ ለክፍል ውይይት በማቅረብ ተማሪዎች ፍትህ የሚጣሱባቸውን ሁኔታዎችና ይህም ሊሆን የሚያስከትሏቸውን ጉዳቶች በተመለከተ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማስቻል። |
| • ማህበራዊ ተቋማት ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፣<br>• የማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሐዊ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች ይገልፃሉ፣ | 4.4 ማህበራዊ ተቋማት (1ክፍለ ጊዜ)<br>4.1 የማህበራዊ ተቋማት ምንነት፣<br>4.2 የማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሃዊነት፣ | • ማህበራዊ ተቋማት ሕብረተሰብን እንዲያገለግሉ የተቋቋሙ ተቋማት ናቸው፣ ተማሪዎች በየተራ ማህበራዊ ተቋማትን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ። በመቀጠልም አገልግሎት አሰጣጣቸው ፍትሀዊ መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያብራሩ ማድረግ፣ ይህን ለማድረግ የሚከብዳቸው ከሆነ ቤተሰቦቻቸውን ወይም ማንኛውንም አዋቂ ሰው ጠይቀው እንዲመጡና እንዲያስረዱ ማድረግና ስለማህበራዊ ተቋማት በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። አቅም በፈቀደ ማህበራዊ ተቋማትን እንዲጐበኟቸው ቢደረግ ለትምህርት ሥርዓት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። |
| • የግብርን ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የግብር ጠቀሜታን ያስረዳሉ፣ | 4.5 ግብር (2ክፍለ ጊዜ)<br>4.5.1 ግብር ምንነትና ጥቅም፣<br>4.5.2 መንግሥት ከግብር በሚያገኘው ገቢ የሚገነባቸው መሠረተ ልማቶች፣ | • ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል መንግሥት ሊየከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት ላይና እነዚህን ተግባራት ለማከናወን መንግሥት ምን እንደሚያስፈልገው እንዲወያዩ ማድረግ። ለምሳሌ መንግሥት ከሚጠበቅበት ተግባር ውስጥ የጤና ጥበቃን ማስፋፋት፣ ትምህርትን ማስፋፋት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋት፣ አገር መከላከል ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።<br>• እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ምን ምን ነገሮች እንደሚያስፈልጉና እነዚህን ነገሮች ከየት ሊያገኛቸው እንደሚችል እንዲገልፁ ማድረግ። አባታቸው/እናታቸው በሚያገኙት ገቢ ቤተሰቡን እንደሚያስተዳድሩ ሁሉ መንግሥትም የሚጠበቅበትን ተግባር የሚያከናውነው |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | በሚሰበሰበው ግብር መሆኑን በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ውይይቱን ወደዛ መምራት ያስፈልጋል። |

## ግምገማ

*ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።*

***ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች*** *የፍትህ ምንነትን ይገልፃሉ፣የፍትህ አስፈላጊነትን ይተነትናሉ፣ከጓደኞቻቸው ጋር ፍትሐዊ የሆኑ ግንኙነትን ይፈጥራሉ፣ የአካባቢ የፍትሕ አካላትንና ተግባራቸውን ይተነትናሉ፣ፍትህ ሊጣሱ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤት ውስጥ አዱሎአዊ አሠራሮች የሚገለፁባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣በቀበሌ ደረጃ አድሎአዊ አሠራሮች የሚገለፁባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣ማህበራዊ ተቋማት ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፣የማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሐዊ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች ይገልፃሉ፣የግብርን ምንነትን ይገልፃሉ፣የግብር ጠቀሜታን ያስረዳሉ፣*

***ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች*** *የፍትህ ምንነትን በምሳሌ ያስረዳሉ፣የፍትህ አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፣የአካባቢ የፍትሕ አካላትንና ተግባራቸውን ይተነትናሉ፣ፍትህ አነዳየጣስ ይታገላሉ፣አዱሎአዊነትን ይቃወማሉሉ፣በቀበሌ ደረጃ አድሎአዊ አሠራሮች የሚገለፁባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣ማህበራዊ ተቋማት ምን እንደሆኑ ያስረዳሉ፣ማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሐዊ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻሉ፣የግብርን ምንነትን ያስረዳሉና ጠቀሜታን ያስረዳሉ፣*

***ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ*** *ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።*

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

**5. የሀገር ፍቅር**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍል ጊዜ 9**

- የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይረዳሉ።
- በዜግነትና በሀገር ፍቅር መካከል ያለውን ግንኙነት ያውቃሉ።
- የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራትን ይለያሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የሀገር ፍቅር ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የሀገር ፍቅር መገለጫ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፣ | 5.1 የሀገር ፍቅር (2ክፍለ ጊዜ)<br>5.1.1 የሀገር ፍቅር ምንነት<br>5.1.2 የሀገር ፍቅር መግለጫ ባህሪያት፣<br>- አካባቢያችን በውል መገንዘብ፣<br>- የጋራ ደህንነትና የሕዝብን ሰላም ሊያናጉ የሚችሉ አፍራሽ ተግባራትን መከላከል፣<br>- ለመንግሥትና ለሕዝብ ሀብት መቆርቆር፣ | • ይህን ትምህርት ለመጀመር ተማሪዎቹን በየተራ ሀገራቸውን ይወዱ እንደሆነ መጠየቅ። በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ለሚመልሱት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ማበረታታት። እንወዳለን የሚሉ ከሆነ ይህ ፍቅራቸው የሚገለጽበትን መገለጫ እንዲዘረዝሩ ማድረግ። የሀገር ፍቅር የማይታይ (Abstract) ሳይሆን የሚጨበጥ የሚዳሰስ መሆን ይገባዋል። ይህም ለሀገር በጐ በመሥራት፣ የሀገር ደህንነትን የሕዝብን ሰላም በመጠበቅና ለሀገር ሀብት በመቆርቆር የሚገለጽ እንደሆነ አንስቶ በማወያየት ተማሪዎች በተባለው ነገር አምነው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማስቻል ያስፈልጋል።<br>• ትምህርቱን የበለጠ ለማስረጽ እንዲያስችልም ሀገሩን የሚወድ ሰው የሚያከናወኗቸው ተግባራት በሚል አንድ ጽሑፍ በማቅረብ በዛላይ ተነስተው ተማሪዎች የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል። |
| • የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራትን ይተነትናሉ፣ | 5.2 የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራት፣ (2ክፍለጊዜ)<br>5.2.1 በጉቦና በዘመድ አዝማድ መሥራት /ሙስና/<br><br>5.2.2 ለሕዝብ ንብረት ብክነት አለመቆርቆር፣ | • ቀደም ባለው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሀገር ፍቅር ምን እንደሆነና መገለጫዎቹም ምን እንደሆኑ አውቀዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራት ናቸው ብለው የሚያስቧቸ ውን በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና በየቡድኑ ተከፋፍለው ያደረጉ ትን ውይይት በአጠቃላይ ውይይት በማዳበር ተማሪዎቹ የራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ዋናው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የቡድንም ሆነ አጠቃላይ ውይይቱ በይዘትነት በተቀመጡ ነጥቦች ዙሪያ እንዲሆን ጥረት |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | 5.2.3 በሰዎች መካከል የመደጋገፍ ባህል መጥፋት፣<br>5.2.4 የምንቸገረኝነትና ምን አገባኝ ስሜት መስፋፋት፣<br>5.2.5 የግል ፍላጎትን ለማግኘት ሕገወጥ በመንገድ መከተል፣<br>5.2.6 በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ አፍራሽ ተግባራት፣ | ማድረግ ነው። |
| • የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• በቤትና በትምህርት ቤት ደረጃ ያሉ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ይዘረዝራሉ፡<br>• ለጋራ መገልገያ መሥሪያ ዎች ሊደረጉ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎች ያብራራሉ፣ | 5.3 የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ምንነት፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>5.3.1 በቤት ውስጥ የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች፣<br>5.3. 2 በትምህርት ቤት የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች፣<br>5.3.3 ለጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፣ | • ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን በቤት ውስጥ የሚገኙ የጋራ መገለገያ መሣሪያዎችን በተመለከተና እንደጋራ ንብረትነታቸው ምን ዓይነት ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እንደሚገባ እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• ሁለተኛውን ቡድን ደግሞ በትምህርት ቤት የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ምንነትና ሊደረግላቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• ሀገር የጋራ እንደመሆኗ መጠን ምን የጋራ ጥንቃቄ ሊደረግላት እንደሚገባ በማወያየት የምዕራፉን ትምህርት ከዚህ የትምህርት ይዘቶች ጋር ማገናኘት ተገቢ ይሆናል። |
| • የድህነትና ኋላቀርነት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመላቀቅ የሚረዱ መንገዶችን ይለያሉ፣ | 5.4 ከድህነትና ኋላቀርነት መላቀቅ፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>5.4.1 የድህነትና ኋላቀርነት መገለጫዎች፣<br>5.4.2 ከድህነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ የመፍትሔ ርምጃዎች<br>5.4.3 ፈጣን የልማት እድገትን ማረጋገጥ፣ | • ኢትዮጵያ ደሀና ኋላቀር ከሚባለው ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ተማሪዎች ይህን እውነታ ይቀበሉ እንደሆነ በየተራ መጠየቅ።<br>• ሁለት ቡድኖችንም በማቋቋም የአንዱ ቡድን አባላት የቤተሰቦቻቸው የወር ገቢ ምን ያህል እንደሆነና ይህም ገቢ የቤተሰቡን ወርሀዊ የምግብ፣ የአልባሳት፣ የሕክምና፣ የትምህርት ቤት ወጪ ይሸፍን እንደሆነ በመጠየቅ ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በአካባቢያቸው በቂ የሕክምና ተቋማት መኖራቸውን በማረጋገጥ ለክፍል ውይይት እንዲያቀርብ ማድረግ። በቂ |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | 5.4.4 የበጐ ፈቃደኝነት፣ አገልግሎት መስጠት፣<br>- የበጐ ፈቃደኝነት ምንነት፣<br>- በቤት በክፍልና በትምህርት ቤት ደረጃ ሊሰጥ የሚችል የበጐ ፈቃድ አገልግሎት፣ | የወር ገቢና የማህበራዊ ተቋማት አለመኖር የምን መገለጫ እንደሆኑ ተማሪዎቹ በስፋት እንዲወያዩ በማድረግ የሀገራቸውን ድህነትና ኋላቀርነት አምነው እንዲቀበሉ ማድረግ። ይህን ድህነትና ኋላቀርንት ለማስወገድም መፍትሔው ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ ተወያይተው የራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማስቻል። ለድምዳሜያቸው እንዲረዳቸው የሚወያዩባቸው ነጥቦች በተጠቀሱት ይዘቶች ዙሪያ እንዲሆን ማድረግ። |
| • የዜግነት ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የብሔራዊ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማን ምንነትና አስፈላጊነትን ይገልፃሉ | 5.5 **ዜግነት (1ክፍለ ጊዜ)**<br>5.5.1 የዜግነት ምንነት፣<br>5.6 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ<br>5.6.1 የሰንደቅ ዓላማና የብሔራዊ የሕዝብ መዝሙር ምንነትና አሰፈላጊነት | • ተማሪዎቹ የኢትዮጵያ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ የሀገሪቱ ዜጐች ናቸው። አሁን ሀገሪቱ ከምትገኝበት የዴሞክራሲ ሥርዓት አንፃር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን ማወያየት።<br>• ተማሪዎቹ ትምህርቱ እንዳይከብዳቸው አስፈላጊው ጥንቃቄ እየተደረገ ዜጐች የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች የተከበሩላቸውና በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያደርጉ መሆናቸውን እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል። እነዚህ የዜግነት መገለጫዎች በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ እየሆኑ መሆኑን ተማሪዎችን በማወያየት ዜግነትን እንዲረዱና ጠቀሜታውንም በራሳቸው እንዲደመድሙ ማስቻል፣ |

## ግምገማ

*ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።*

***ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች*** *የሀገር ፍቅር ምንነትን ይገልፃሉ፣የሀገር ፍቅር መገለጫ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፣የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራትን ይተነትናሉ፣ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ምንነትን ይገልፃሉ፣ በቤትና በትምህርት ቤት ደረጃ ያሉ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ይዘረዝራሉ፡ ለጋራ መገልገያ መሥሪያዎች ሊደረጉ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎች ያብራራሉ፣ የድህነትና ኋላቀርነት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመላቀቅ የሚረዱ መንገዶችን ይለያሉ፣የዜግነት ምንነትን ይገልፃሉ፣የብሔራዊ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማን ምንነትና አስፈላጊነትን ይገልፃሉ*

## 5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የሀገር ፍቅር ምንነትን በተገባር ያሳያሉ፣የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራትን ይታገላሉ፣ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ይንከባከባሉ፣ በቤትና በትምህርት ቤት ደረጃ ያሉ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ከጉዳት ይጠብቃሉ፡ ፣ የድህነትና ኋላቀርነት ይታገላሉ፣፣ በዜግነትና በሃገር ፍቅር መካከል ያለውን ትስስር ያስረዳሉ፣የብሔራዊ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማን ትርጉም ይገልጻሉ።

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**6. የኃላፊነት ስሜት**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 12**

- የኃላፊነት ምንነትን ይረዳሉ።
- የተለያዩ የኃላፊነት ዓይነቶችን ያውቃሉ።
- ተግባርን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት በመፈፀም በየደረጃው የዜግነት ኃላፊነትን ይወጣሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • የኃላፊነት ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታን ያስረዳሉ፣ | 6.1 ኃላፊነት የመውሰድ ግዴታ ምንነት፣<br>**(2ክፍለ ጊዜ)**<br>6.1.1 በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች ኃላፊነትን መውሰድ፣<br>6.1.2 በቤት ውስጥ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች ኃላፊነትን መውሰድ፣ | • ተማሪዎች ኃላፊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በየተራ እንዲያብራሩ ማድረግ። በማስከተልም በቡድን በመከፋፈል በቤትና በትምህርት ቤት ሊኖሩ የሚችሉ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ለቡድኖቹ በመስጠት በተሰጣቸው ኃላፊነቶች ላይ የነሱ ግዴታ ምን ሊሆን እንደሚገባው እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• ይህን የቡድን ውይይት በአጠቃላይ ውይይት እንዲዳብር ማድረግና ኃላፊነት የመውሰድ ግዴታን አስመልክቶ ተማሪዎች በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የቃል ኪዳን ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• በቤተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገቡትን ቃል ማክበር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፣ | 6.2 የቃል ኪዳን ምንነትና አስፈላጊነት፣<br>**(1ክፍለ ጊዜ)**<br>6.2.1 በቤትና በት/ቤት ቃልን | • እያንዳንዱ ተማሪ በትምህርቱ ውጤታማ እንዲሆን፣ ለቤተሰቡ ወይም ለሀገሩ አንድ ነገር እንዲፈጽም ቃል ኪዳን እንዲገባ ማድረግ። ይህም ቃል ኪዳን ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እንዲያስረዱ በማድረግ ቃልን አክብሮ የመገኘት ኃላፊነት ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | አክብሮ የመገኘት ኃላፊነት፣ | |
| • የቅንነት፣ የታማኝነትና የሀቀኝነት ምንነት ያብራራሉ፣<br>• በደረጃቸው የሚያከናውኗ ቸውን ተግባራት በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ለማከናወን ጥረት ያደርጋሉ፣ | 6.3 የቅንነት፣ የታማኝነትና የሀቀኝነት ምንነት፣<br>(1ክፍለ ጊዜ)<br>6.3.1 ማንኛውንም ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ማከናወን፣ | • ቅንነት፣ ታማኝነትና ሀቀኝነት እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግ።<br>• ይህን ካስረዱ በኋላ እነሱ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ቅንነት፣ ታማኝነትና ሀቀኝነት እንዴት ሊገለፁ እንደሚችሉ እንዲወያዩና አጠቃላይ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊነቶችን የመወጣት አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣<br>• በደረጃቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች ይወጣሉ፣ | 6.4 ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት፣<br>(2ክፍለ ጊዜ)<br>6.4.1 በቤተሰብ ውስጥ፣<br>6.4.2 በትምህርት ቤት ውስጥ፣<br>6.4.3 በማህበራዊ ሕይወት፣ | • የክፍሉን ተማሪዎች በሦስት ቡድኖች መክፍለ፣ ለአንዱ ቡድን በቤት ውስጥ ተማሪዎች ያሉባቸውን ኃላፊነቶች፣ ለሁለተኛው ቡድን በትምህርት ቤት ተማሪዎችያሉባቸውን ኃላፊነቶች፤ ለሦስተኛው ቡድን በሰፈር ውስጥ ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነቶች ያሉባቸው ኃላፊነቶች ምን እንደሆኑና እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ እንዲወያዩ ማድረግ። የቡድን ውይይታቸውንም በክፍል ውስጥ ውይይት በማጠናከር ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት ላይ የጋራ ድምዳሜ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የተፈጥሮ ሀብትን የታሪካዊ ቅርስ ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ያስረዳሉ፣ | 6.5 የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርስ ምንነት፣<br>(2ክፍለ ጊዜ)<br>6.5.1 የተፈጥሮ ሀብቶችን ማልማት፣<br>6.5.2 ታሪካዊ ቅርሶችን | • በመጀመሪያ ሁሉም ተማሪዎች የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶችን ምን እንደሆኑ አካባቢያዊ ምሳሌዎችን እየሰጡ እንዲገልፁ ማድረግ።<br>• እነዚህን ሀብቶችና ቅርሶች በነሱ ደረጃ እንዴት ሊያሚኗቸውና ሊንካባከቧቸው እንደሚችሉ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማድረግ። በተቻለ መጠን የሚካሄደው ውይይት ኃላፊነትን ከመወጣት ጋር እንዲያያዝ በማድረግ ተማሪዎቹ የተፈጥሮ ሀብትንና ታሪካዊ ቅርስን የመንከባከብ ኃላፊነትን የበለጠ እንዲረዱ ሊያስችላቸው ይገባል። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | መንከባከብ፣ | |
| • ራሳቸውን ከኤች አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣<br>• የኤች አይ.ቪ/ኤድስን ምንነት ይገልፃሉ፣<br>• በሽታው የሚተላለፍባቸ ውን መንገዶች በደረጃ ቸው ይዘረዝራሉ፣<br>• በሽታው በልጆች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ | 6.6 የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ፣<br>6.6.1 በሽታው በልጆች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣(**2ክፍለ ጊዜ**)<br>6.6.2 እራስን ከበሽታው መጠበቅ፣<br>- ሌሎች ሰዎች በተጠቀሙ ባቸው ስለታም መሣሪያ ዎች አለመጠቀም፣ | • የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚባልና መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ በየትኛውም ክልል የሚገኝ መሆኑን መግለጽ። በሽታው እናትና አባትን በሚገድልበት ጊዜ ልጆችን ያለአሳዳጊ ስለሚያስቀራቸው በልጆች ኑሮ ላይ በትምህርታቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል።<br>• ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ወላጆቻቸው በኤድስ የሞቱባቸው ልጆችን ያውቁ እንደሆነና እነዚህ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ኑሮ ምን እንደሚመስል እንዲያብራሩ ማድረግ።<br>• በሽታው ወደ ህፃናትሊተላለፍ የሚችለው በዋንኛነት ሌሎች ሰዎች በተገለገሉባቸው ስለታም መሣሪያዎች ሲጠቀሙ መሆኑን በመግለጽ፤ ይህ እንዳይሆን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ቃል ኪዳን መግባት በሚመስል መልኩ እንዲያስረዱ ማድረግ። |

## ግምገማ

*ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።*

***ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የኃላፊነት ምንነትን ይገልፃሉ፣ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታን ያስረዳሉ፣የቃል ኪዳን ምንነትን ይገልፃሉ፣ በቤተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገቡትን ቃል ማክበር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፣የቅንነት፣ የታማኝነትና የሀቀኝነት ምንነት ያብራራሉ፣በደረጃቸው የሚያከናውኗ ቸውን ተግባራት በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ለማከናወን ጥረት ያደርጋሉ፣በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊነቶችን የመወጣት አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣የተፈጥሮ ሀብትን የታሪካዊ ቅርስ ምንነትን ይገልፃሉ፣የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ያስረዳሉ፣በደረጃቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች ይወጣሉ፣ራሳቸውን ከኤች አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣የኤች አይ.ቪ/ኤድስን ምንነት ይገልፃሉ፣በሽታው የሚተላለፍባቸ ውን መንገዶች በደረጃ ቸው ይዘረዝራሉ፣በሽታው በልጆች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገልፃሉ፣*

## 5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**

የኃላፊነት ይቀበላሉ፣ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታን ያስረዳሉ፣የቃል ኪዳንን ያከብራሉ፣በቤተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገቡትን ቃል ያከብራሉ፣የቅንነት፣ የታማኝነትና የሀቀኝነት ምንነት በምሳሌ ይገልጻሉ፣፣በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊነቶችን ይወጣሉ፣የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣በደረጃቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች ይወጣሉ፣ራሳቸውን ከኤች አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣፣በሽታው የሚተላለፍባቸ ውን መንገዶች በደረጃ ቸው ይገልጻሉ፣በሽታው በልጆች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

7. ጠንካራ የሥራ ባህል

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣ የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8

- ጠንካራ የሥራ ባህል ምንነትን ይረዳሉ።
- የጠንካራ የሥራ ባህል ምንነት ያውቃሉ፣
- የሙያ ሥነ-ምግባርን ምንነት ያውቃሉ፣
- የሥራ ክቡርነትን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ሥራን ፈጥሮ የመኖር አስፈላጊነትን በምሳሌዎች ይገልፃሉ፣<br>• ሥራ ክቡር መሆኑን ያስረዳሉ፣ | 7.1 ሥራን መፍጠር ማለት ምን ማለት ነው? ፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>7.1.1 ሥራን ፈጥሮ ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሁኔታዎች፣<br>- የራስ ተነሳሽነትና ጥረትን ማዳበር፣<br>- የሥራን ክቡርነት መረዳት፣ | • በመኖሪያ አካባቢያቸው በመንግሥት ወይም በግለሰብ ተቀጥረው ሳይሆን የራሳቸውን ሥራ (ለምሳሌ ንግድ፣ እንጨት ሥራ፣ የብረታ ብረት ሥራ፣ ሽክላ ሥራ ወዘተ) ፈጥረው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ሰዎችን እንዲገልፁ ማድረግ።<br>• እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው መኖር ያስቻላቸው ጉዳይ ምን እንደሆነ በቡድን ውይይታቸው ውስጥ የራስን ሥራ ፈጥሮ መኖር ወይስ ተቀጣሪ ሆኖ መሥራት ይሻላል የሚለውን አካተው እንዲነጋገሩ ማድረግ።<br>• እነዚሁ ቡድኖች በአካባቢያቸው የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው የሚኖሩ ሰዎችን እንዲጐበኙና ለምን የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው መኖር እንደፈለጉ፣ ውጤታማ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን፣ ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች ወዘተ በሚመለከት እንዲያነጋግሯቸውና የሚያገኙትን መልስ ክፍል ውስጥ በማምጣት እንዲወያዩበት ማድረግ። ውይይታቸው የሥራን ክቡርነትና ሥራን ፈጥሮ መኖር አስፈላጊነት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ተገቢ ይሆናል። |
| • ሳይሰሩ መብላትን ምንነት፣ ጐጂነትና አስነዋሪነት ይገልፃሉ፣ | 7.2 ሳይሰሩ መብላት፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>7.2.1 ሳይሰሩ መብላት ምንድን ነው?<br>7.2.2 ሳይሰሩ መብላት የሚያስከትሏቸው ችግሮች<br>- በሰዎች መጠላትና | • «ሳይሰሩ መብላት ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ ነው?» በሚል ጭብጥ በክፍል ውስጥ ክርክር እንዲካሄድ ማድረግና ከተሰነዘሩ ሀሳቦችን በመነሳት በክፍል ውስጥ የጋራ ውይይት ማድረግ።<br>• ሳይሰሩ መብላት አስነዋሪና አፀያፊ ተግባር መሆኑን እንዲሁም ሰዎች እንዲጠሉን የሚያደርግ መሆኑን ተማሪዎቹ እራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። እንዲሁም በነሱ ደረጃ ሊያውቁት የሚገባው ሌላው ነገር ሰውነታችን ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል በቂ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው ሲሆን ይህ እንቅስቃሴ በማይኖርበት ጊዜ ለበሽታ ልንዳረግ እንደምንችል ነው። ስለዚህ ሥራን አለመሥራት አቅም ከማሳጣት |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | አለመከበር፣<br>7.2.3 ሳይሰሩ መብላትን መጸየፍ፣ | ጀምሮ ብዙ ጉዳቶች እንዳሉት እንዲገነዘቡ ማድረግ። |
| • የሚሰሩትን ሥራና የሚሰሩበትን ቦታ መምረጥ የማንኛውም ሰው መብት መሆኑን በምሳሌ ያስረዳሉ፣ | 7.3 የሥራ መብቶች፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>7.3.1 የፈለጉትን ሥራ በፈለጉት ቦታ የመሥራት መብት፣<br>7.3.2 የግል ንብረት የማፍራት መብት፣ | • እያንዳንዱ ተማሪ ወደፊት ምን ዓይነት ሥራ ሰርቶ መኖር እንደሚፈልግና ይህንን የሱ ምርጫ የሆነን ሥራ የት ቦታ ወይም ሀገር ሆኖ መሥራት እንደሚሻ እንዲገልፅ ማድረግ።<br>• ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለባቸውና ይህን ሥራ የት ቦታ ሆነው መሥራት እንዳለባቸው መንግሥት ወይም አንድ ሌላ አካል ቢወስንላቸው ጥሩ ወይም መጥፎ እንደሆነ እንዲወያዩ ማድረግ። ውይይቱ የሚሠሩትን ሥራና የሚሠሩበትን ቦታ የመምረጥ መብት የግለሰቡ የራሱ መሆኑንና ይህም በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት እውቅና ያለው መሆኑ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ። |
| • የሙያ ሥነምግባር ምንነትን ያስረዳሉ፣ | 7.4 ሙያና የሙያ ሥነምግባር ምንነት፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>7.4.1 ለሙያው ደንብና የሥራ መርሆ መገዛት፣<br>7.4.2 የሙያ ችሎታን ማዳበር፣<br>7.4.3 በሙያው ውጤት በሚጠቀሙ ወገኖች መታመን፣ | • ማንኛውም ተግባር የራሱ የሆነ የሥነምግባር መመሪያዎች አሉት፣ ይህን በተመለከተ በሕግ የበላይነት ምዕራፍ ሥር በትምህርት ቤት ደረጃ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ሥነምግባር ምን እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያውቁት ተደርጓል። ይህን ትምህርት በመከለስ መልክ ተማሪዎቹ ከነሱ የሚጠበቁ ሥነምግባሮች ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ ማድረግ።<br>• ከዚያም ለነዚህ ሥነምግባሮች ራስን ማስገዛት ለምን እንደሚያስፈልግ እንዲወያዩ ማድረግ። ለምሳሌ ያህልም አንድ ነጋዴን በመውሰድ ጥሩ ዕቃ ነው እያለ ሁልጊዜ የተበላሸ ዕቃ የሚሸጥላቸው ከሆነ ከዚህ ነጋዴ ዕቃ ይገዙ ወይም አይገዙ እንደሆነ እንዲያስረዱ ማድረግ።<br>• ከዚህም በምንም ዓይነት ሥራ የሙያ ሥነምግባር የሌለው ሰው ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል ተማሪዎቹ ግንዛቤ እንዲወስዱ ማድረግ። በሙያ ሥነምግባራቸው የተመሰገኑ ሰዎችን ያውቁ እንደሆነም እንዲጠቅሱ በማድረግ ከላይ የተገለጸውን ጉዳይ ማጠናከር። |

## ግምገማ

*ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።*

- ***ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች*** *ሥራን ፈጥሮ የመኖር አስፈላጊነትን በምሳሌዎች ይገልፃሉ፣ሥራ ክቡር መሆኑን ያስረዳሉ፣ሳይሰሩ መብላትን ምንነት፣ ጉጂነ ትና አስነዋሪነት ይገልፃሉ፣የሚሰሩትን ሥራና የሚሰሩበትን ቦታ መምረጥ የማንኛውም ሰው መብት መሆኑን በምሳሌ ያስረዳሉ፣የሙያ ሥነምግባር ምንነትን ያስረዳሉ፣*
- ***ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች*** *ሥራን ፈጥሮ የመኖር አስፈላጊነትንያስረዳሉ፣ሥራ ክቡር መሆኑን ያስረዳሉ፣ሳይሰሩ መብላትን ይፀየፋሉ፣ ፣የሚሰሩትን ሥራና የሚሰሩበትን ቦታ መምረጥ የማንኛውም ሰው መብት መሆኑን በምሳሌ ያስረዳሉ፣የሙያ ሥነምግባር ይገልፃሉ፣*

***ውጤታቸው ዝቅተኛ*** *የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።*

## 8. ራስን መቻል

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- ራስን የመቻል ምንነትን ይረዳሉ፣
- በራስ የመተማመን ጠቀሜታን ይረዳሉ፣
- ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን ለምን እንደሚጠቀም ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ራስን የመቻል ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• በራስ መተማመን ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ያስረዳሉ፣ | 8.1 ራስን የመቻል ምንነት፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>8.1.1 ትምህርትን ጠንክሮ መማር፣<br>8.1.2 ፈተናን እራስን ችሎ መሥራት፣<br>8.1.3 በአቅም የሚሠሩ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ራስን ችሎ መሥራት፣<br>8.2 በራስ መተማመን፣<br>8.2.1 በራስ መተማመን ምንድን ነው? | • በነሱ ደረጃ ትኩረት የሚሻውና ራስን የመቻል ጉዳይ የሚገለፀው ለትምህርታቸው ልዩ ትኩረት ሰጥተው መማራቸው፤ እንዲሁም የሚሰጣቸውን ፈተና ሳይኮርጁ ራሳቸውን ችለው በመሥራት ነው። ስለሆነም ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ጠንክረው መማራቸው የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>• በአካባቢው ራስን በመቻል/ጥሩ በመማራቸው፤ ጥሩ ገበሬ በመሆናቸው፣ ጥሩ ነጋዴ፣ ጥሩ የእደጥበብ ሰው፣ ወዘተ በመሆናቸው ቤተሰቦቻቸውን፣ አካባቢያቸውንና ለሀገር ጠቀሜታ የሰጡ ግለሰቦች እንዴት አርአያ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲገልፁ ማድረግና ራስን የመቻል ጉዳይን እንዲያደንቁ ማድረግ። |
| • በአቋም የመጽናት ምንነትና አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፣ | 8.3 በአቋም መጽናት፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>8.3.1 የራስን ነፃ አቋም መያዝ፣<br>8.3.2 በሚገባ አመዛዝኖ መወሰን፣<br>8.3.3 ያመኑበትን ሀሳብና አመለካከት በነፃነት ማራመድ፣ | • እያንዳንዱ ተማሪ ወደፊት ምን መሆን እንደሚሻ እንዲገልጽ ማድረግ። ይህን ዓላማቸውን ለማሳካት ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሁ እንዲያስረዳ ማድረግ። የሚሰጡት አስተያየት ለምሳሌ ተማሪ እስከመጨረሻው በትምህርቱ ገፍቶ ውጤታማ እንዲሆን ጥንካሬና የአቋም ፅናት ሊኖረው እንደሚገባ፤ አንድ ተማሪ ዛሬ አልተመቸኝም ወይም እንደምፈልገው አልተመቻቸልኝም ብሎ በጊዜያዊ ችግር ትምህርቱን የሚያቋርጥ ከሆነ የዓላማ/የአቋም ፅናት የለውምና የትም ሊደርስ አይችልም። ነገር ግን ሁሉንም ችግሮች ችሎ በትምህርቱ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | • ውጤታማ መሆን አለብኝ ብሎ በዓላማ ፅናት ከተነሳ ሀሳቡ የማይሳካበት ምንም ምክንያት ሊኖር እንደማይችል የሚገልጽ መሆን አለበት። <br>• በሌላ በኩል ውሣኔዎችን ተማሪዎች እንዴት እንደሚወስኑ እንዲገልፁ ማድረግ። ለምሳሌ ዛሬ አልጫወትም ጥናት ነው የማጠናው ቢሉ እዚህ ውሳኔ ላይ እንዴት እንደሚደርሱ እንዲያስረዱ ማድረግ። ዋናው ቁምነገር ማናቸውንም ውሳኔ በሚወስኑበት ጊዜ መጀመሪያ በሚገባ አመዛዝነው መሆን ያለበት ሲሆን፤ አንዴ ከወሰኑ በኋላ ግን ባመኑበት ሀሳብ መጽናት የሚገባቸው መሆኑን እራሳቸው እንዲያምኑ መደረግ አለበት። |
| • ስለራሳችን የሚኖ ርን የተሳሰተ ግንዛቤ የሚያስከ ትላቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣ | 8.4 ስለራሳችን የሚኖረን የተሳሳተ ግንዛቤ የሚገለጹባቸው ባህሪያት፣(**2ክፍለ ጊዜ**)<br>8.4.1 የበላይነት ስሜት<br>8.4.2 የበታችንት ስሜት<br>8.4.3 ከሌሎች ጋር አለመጣጣም፣<br>8.4.4 ለሚሰሩት ሥራ ትኩረት አለመስጠት፣<br>8.4.5 በራስ አለመተማመን፣ | • ሰዎች ስለራሳቸው ሊኖሯቸው ስለሚችሉ የተለያዩ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን አስመልክቶ ክልላዊ ምሳሌዎችን ማቅረብ። ለምሳሌ #ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም$ ይባላል። አንዱ ሰው ደፋር ስለሆነ ሁልጊዜ የሚፈልገው ነገር ይሳካለታል ወይ? እንደነዚህ ያሉ ምሳሌዎችን በማንሳትና በማወያየት ሰዎች ስለራሳቸው የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን እንደሚይዙ ተማሪዎቹ እንዲረዱ ማድረግ። <br>• በሌላ በኩል አንዳንድ ሰዎች እራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ ያህልም ተማሪዎች #እኔ ከክፍል አንደኛ መውጣት አልችልም ምክንያቱም ትምህርቱ ካባድ ነው$ ይላሉ። ይህ አባባል ትክክለኛ ነው ወይ? በዚህ ላይ ተማሪዎች ውይይት እንዲያደርጉ መጋበዝ። ውይይቱም እንዲህ ዓይነት አመለካከት የተሳሳተና በራስ ካለመተማመን የሚመነጭ የበታችነት ስሜት እንጂ ማንም ተማሪ ጠንክሮ ከሰራና ካጠና አንደኛ የማይወጣበት ምክንያት ሊኖር እንደማይችል የሚያመላክት መሆን አለበት፣ <br>• ልክ አንደኛ አልወጣም እንዳለው ተማሪ በአንድ ወቅት አንደኛ የወጣ ተማሪ በድሮው ዝና ብቻ ምንም ለትምህርቱ ትኩረት ሳይሰጥ አሁንምአንደኛ እወጣለሁ ብሎ ዋልጌ ቢሆን ይህም ስለራስ የተሳሳተ ግንዛቤ ነውና ተማሪዎቹ ሊወያዩባቸው ይገባል። እራስን ከሚገባው በላይ ከፍ ማድረግ፤ እንዲሁም ዝቅ ማድረግ፣ ከሰዎች ጋር ለሚኖረን ግንኙነት እንቅፋት ነው። እንዲሁም ለምንሰራው ሥራ ትኩረት እንዳንሰጥ የሚያደርግ ነው። ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | ተማሪዎች እንዲወያዩና በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የራስን ችሎታ ማወቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣<br>• ከሌሎች ልምድና ዕውቀትን ለመቅሰም ጥረት ያደርጋሉ፣<br>• የኮንትሮባንድ ንግድ ምንነትና የሚያስከትለውን ጉዳት ይገልፃሉ | 8.5 የራስን ችሎታ በማወቅ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የመሆን ጠቀሜታ፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>8.5.1 የሀገርን እድገትና ብልጽግና መሥራት፣<br>8.5.2 የሀገርን እድገትና ብልጽግና የሚጎዱ ተግባራት<br>- የኮንትሮባንድ ንግድ፣<br>• የኮንትሮባንድ ንግድ ምንነት፣ | • የራስን ችሎታ ማወቅ ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲወያዩበት ማድረግ።<br>• ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ወይም እህትና ወንድሞቻቸው ሊማሩ የሚችሏቸው ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን እንዲገልፁ ማድረግ። ለምሳሌ ሁሉም ተማሪ የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ይዘቶችን እኩል ላይረዳ ይችላል። በዚህ ጊዜ ከመምህራቸው ከመረዳታቸው ባሻገር የክፍል ጓደኞቻቸውን ወይም ቤተሰባቸውን ጠይቀው ሊረዱ ይችላሉ። ያላወቁትን ነገር ጠይቆ መረዳት ብልህነት ብቻ ሳይሆን ያዋቂነትም ምልክት ነውና ለላቀ ውጤት ሊያበቃ ይችላል። በሀገርም ደረጃ እንደዚሁ ነው። እንዲህ እያለ ነው ሥልጣኔ የተስፋፋው። ስለዚህ የራስን ችሎታ በማወቅ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን ለሀገርም እድገት የሚበጅ ጉዳይ ነው። ይህንን ሀሳብ ተማሪዎች እንዲወያዩና የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ።<br>• በሌላ በኩል ተማሪዎችን ስለኮንትሮባንድ ንግድ እንዲረዱ በመጀመሪያ መግለጫ መስጠት። የኮንትሮባንድ ንግድ ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ሳይከፍሉ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚደረግ ሕገወጥ የንግድ ተግባር ነው። ትምህርቱ የበለጠ ተጨባጭነት እንዲኖረው ትምህርቱን በድራማ መልክ ማቅረብና ተማሪዎች ከድራማው ምን እንደተገነዘቡ እንዲወያዩ ማድረግ። |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ራስን የመቻል ምንነትን ይገልፃሉ፣በራስ መተማመን ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ያስረዳሉ፣በአቋም የመጽናት ምንነትና አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፣ስለራሳችን የሚኖ ርን የተሳሰተ ግንዛቤ የሚያስከ ትላቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣የራስን ችሎታ ማወቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣ከሌሎች ልምድና ዕውቀትን ለመቅሰም ጥረት ያደርጋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**  ራስን የመቻልን በምሳሌ ያስረዳሉሉ፣በራስ መተማመን ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ያስረዳሉ፣በአቋም የመጽናት ምንነትና አስፈላጊነትን በምሳሌ ያስረዳሉ፣፣የራስን ችሎታ ማወቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምሳለሌ ይገልፃሉ፣ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ ይሆናሉ፣ከሌሎች ልምድና ዕውቀትን ይቀስማሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ**  **የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 9. የቁጠባ ባህል

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበለት ክፍል ጊዜ 6**

- የቁጠባን ምንነት ይረዳሉ።
- የቁጠባ ባህልን ማዳበር እራስን መቻል እንደሚያገለግል ይረዳሉ።
- በአካባቢያቸው የቁጠባ ባህልን ማዳበር ለምን እንደሚያስፈልግ ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የቁጠባ ምንነትንና ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 9.1 ቁጠባ (2ክፍለ ጊዜ)<br>9.1.1 የቁጠባ ምንነት፣<br>9.1.2 የቁጠባ ዓላማዎች፣<br>- የሌሎች ጥገኛ ላለመሆን፣<br>- ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን ችግር ለመቋቋም፣ | • ተማሪዎች ቁጠባ ምን እንደሆነና የሚቆጠበውስ ነገር ምን እንደሆነ እንዲያስረዱ ማድረግ፣። ከዚህም በመነሳት በየዓመቱ ከሚያገኘው ገቢ የሚቆጥብ ገበሬ ወይንም ነጋዴ ወዘተ ሊገጥመው የሚችለውን ችግር ከመቋቋም ባሻገር/ቢታመም ይታከማል፤ ድርቅ ቢመጣ ከችግር ይወጣበታል ወዘተ/ እያደር የተሻለ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። ለምሳሌ ገበሬ ወደ ሃብታም ገበሬነት፤ ነጋዴ ወደ ሃብታም ነጋዴነት፤ ወዘተ ሊሸጋገር እንደሚችል በማስገንዘብ ተማሪዎች በጉዳዩ ላይ ተወያይተው የቁጠባን ምንነትና ዓላማውንም በራሳቸው እንዲረዱ ማድረግ። |
| • በእቅድና በአቅም ልክ የመመራት ምንነትን ያብራራሉ፣<br>• በእቅድና በአቅም ልክ ይኖራሉ፣ | 9.2 በእቅድና በአቅም ልክ መመራት፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>9.2.1 በእቅድና በአቅም ልክ የመመራት ምንነት፣<br>9.2.2 በእቅድና በአቅም ልክ መኖር፣ | • እቅድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች በየተራ እንዲገልጹ ማድረግ። የበለጠ ግልጽ እንዲሆንም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የጥናት እቅድ እንዲያወጡ ማድረግ።<br>• ሳምንታዊ የጥናት እቅድ ማዘጋጀት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ የቡድን አባላት እንዲገልፁ ማድረግ። በእቅድ የምንመራ ከሆነ ከአቅማችን በላይ ለማቀድ ስለማንችል በእቅድ መመራት በአቅማችን ልክ እንድንኖር የሚያስችለን መሆኑን ተማሪዎቹን ማወያየትና የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ።<br>• እንዲሁም በአቅም ልክ መመራት ለምን እንደሚያስፈልግ ተማሪዎች እንዲወያዩና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | 9.3 በቤተሰብ ውስጥ ቁጠባን የሚፃረሩ ተግባራት፣ (2ክፍለ ጊዜ)<br>9.3.1 የተንዛዛ ሠርግ፣<br>9.3.2 ተዝካር ሰደቃ፣<br>9.3.3 የማህበራት ድግስ፣<br>9.3.4 ከልክ ያለፈ የበዓል አከባበር፣<br>9.3.5 ጠጪነት፣<br>9.3.6 የተለያዩ ሱሶች፣ | • ሠርግ፣ ተዝካር፣ አካባቢያዊና ብሔራዊ በዓላትን ተማሪዎች እንዲዘረዝሩዋቸው ማድረግ። ለነዚህ በዓላት ቤተሰቦቻቸው ምን ያህል ወጪ እንደሚያወጡ እራሳቸው እንዲናገሩ፤ ወይም ቀደም ብሎ የቤት ሥራ በመስጠት ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው እንዲመጡና ወጪዎቹን እንዲያስረዱ ማድረግ። እነዚህ ወጪዎች በኑሮ ላይ የሚያስከትሏቸውን ተጽዕኖ /በሬ መሸጥ፤ አላስፈላጊ ብድር ውስጥ መግባት ወዘተ/ እንዲወያዩባቸው ማድረግና ሊወሰዱ በሚገቧቸው እርምጃዎች ላይ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ።<br>• ከዚህም ባሻገር የተለያዩ ሱሶች በወጪ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ በቀላል ምሳሌ (ለምሳሌ የሲጃራና የጫት ሱሰኛ ከመደበኛ ወጪው ባሻገር ተጨማሪ ወጪ የሚያወጣ መሆኑን) በማስረዳትና ተማሪዎች እንዲወያዩበት በማድረግ ሱሶች ሊወገዱ እንደሚገቡ ተማሪዎች የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባ ምንነትንና ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣በእቅድና በአቅም ልክ የመመራት ምንነትን ያብራራሉ፣
በእቅድና በአቅም ልክ ይኖራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባ ምንነትንና ዓላማዎችን ያስረዳሉ፣በእቅድና በአቅም ልክ ይመራሉ፣ በእቅድና በአቅም ልክ ይኖራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

## 10. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 6**

- የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምንነት ያውቃሉ።
- ሕዝባዊ ተሳትፎ ለእድገት ያለውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- በትምህርት ቤትና በአካባቢ የዲስፕሊን፣ የፅዳትና የልማት ተግባራት ላይ የመሳተፍን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• በክፍል ደረጃ በሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፣ | 10.1. የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምንነት፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>-በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት ንቁተሳትፎ ማድረግ፣<br>- የክፍል አለቃን በንቃት መምረጥ፣<br>- የክፍል ጽዳትን መጠበቅ፣<br>- የክፍል ደንብና ሥርዓት ማክበርና እንዲከበር ማድረግ፣ | • እያንዳንዱ ተማሪ እነሱን በተመለከተ ንቁ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጽ ማድረግ።<br>• ንቁ ተሳትፎን ግልጽ ለማድረግም ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን በመክፈል በክልላቸው ውስጥ የነሱን ንቁ ተሳትፎ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ። ይህንንም የቡድን ውይይት በክፍል ውስጥ የጋራ ውይይት በማጠናከር ተማሪዎች ከሚጠበቅባቸው ተሳትፎዎች ውስጥ የክፍላቸውን ጽዳት ባግባቡ መጠበቅ፣ የክፍልን ደንብና ሥርዓት በማስከበር ሒደት በያገባኛል ስሜት መሳተፍና የክፍል አለቃቸውን በንቃት መምረጥ እንደሚገባቸው የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ። |
| • የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነትና ጠቀሜታዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 10.2 የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት፣ **(2ክፍለ ጊዜ)**<br>10.2.1 በትምህርት ቤት | • ቀደም ባለው ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከነሱ የሚጠበቀውን ተሳትፎ እንዲያውቁ ተደርገዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለምን እንደሚያስፈልግ ሊያውቁ ይገባል። ስለሆነም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል በትምህርት ቤት ደረጃ የእነሱ ተሳትፎ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እንዲወያዩ ማድረግ። ለምሳሌ |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | በሚቋቋመው ልዩ ልዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ለመሳተፍ፣<br>10.2.2 ትምህርት ቤትን ለማስዋብ፣<br>- በችግኝ ተከላ መሳተፍ፣ | በትምህርት ቤት ለሚቋቋሙ ክበባትና ኮሚቴዎች መሳተፍ ለምን እንደሚያስፈልግ እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣ | 10.3 የሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶች፣<br>10.3.1 በትምህርት ቤት ውስጥ ተሳትፎ የሚፈልጉ ጉዳዮች፣ (1ክፍለ ጊዜ)<br>10.3.2 በህብረተሰብ ፍላጐት የሚካሔዱ ማህበራዊ ተሳትፎዎች፣ | • በዚህ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች ሁለቱን የተሳትፎ ዓይነቶች ካወቁ በቂ ይሆናል። እነዚህም በትምህርት ቤትና በህብረተሰብ ደረጃ ሊደረጉ የሚገቡ ተሳትፎዎች ናቸው። ስለዚህ ተማሪዎቹን በሁለት በመክፈል በትምህርት ቤት ውስጥ በተሳትፎ ሊከናወኑ የሚገቡ ጉዳዮችን እንዲሁም በህብረተሰብ ፍላጐት ላይ ተመስርቶ የሚካሄዱ ማህበራዊ ተሳትፎዎችን በመለየት እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• በዚህ ውስጥ የነሱ ተሳትፎ ምን መሆን እንደሚገባም እንዲወያዩ ማድረግ። ለምሳሌ በትምህርት ቤት ውስጥ ተሳትፎ የሚፈልጉ ጉዳዮች የትምህርት ቅጥር ጊቢን ማስዋብ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በህብረተሰብ ፍላጐት የሚካሔዱ ማህበራዊ ተሳትፎ ዎች የአቅመ ደካሞችን ቤቶች ማደስ ሊሆን ይችላል። ተማሪዎቹ ለውይይቱ መረጃ የበለጠ የሚፈልጉ ከሆነ ቤተሰቦቻቸ ውን ወይም በጉዳዩ ላይ መረጃ ሊሰጥ የሚችል ማናቸውንም ሰው እንዲጠይቁ ማድረግ። |
| • የሲቪክ ማህበራት ምንነትን ያብራራሉ፣<br>• በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉት ክበባት በመሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ፣<br>• በትምህርት ቤት የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣ | 10.4 የሲቪክ ማህበራት፣ (1ክፍለ ጊዜ)<br>10.4.1 የሲቪክ ማህበራት ምንነት፣<br>10.4.2 በሲቪክ ማህበራት ተግባራዊ ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊነት፣ | • በመጀመሪያ ሲቪክ ማህበራት ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ ማድረግ። የሚያውቁ ከሆነ ስለ ሲቪክ ማህበራት ማብራሪያ መስጠት። ይህን ከተረዱ በሲቪክ ማህበራት ተደራጅቶ መሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን ወይም አስፈላጊ አለመሆኑን በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና አስፈላጊ የሚያደርገውም ምን እንደሆነ እንዲያስረዱ ማድረግ።<br>• የቡድን ውይይታቸውን በክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪ በሚሳተፍበት ቡድኖቹ እንዲያቀርቡትና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

**ግምገማ**

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣በክፍል ደረጃ በሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፣የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነትና ጠቀሜታዎችን ይዘረዝራሉ፣የሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣የሲቪክ ማህበራት ምንነትን ያብራራሉ፣በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉት ክበባት በመሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤት የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎን በምሳሌ ያስረዳሉ፣በክፍል ደረጃ በሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፣የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነትና ጠቀሜታዎችን በተግባር ያሳያሉ፣የሲቪክ ማህበራት ምንነትን ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉት ክበባት ይሳተፋሉ፣በትምህርት ቤት የተለያዩ የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 11. እውቀትን መሻት

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍል ጊዜ 8**

- ዕውቀትን መሻት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ።
- የዕውቀት ባለቤት መሆን ለራስ ኑሮ መሻሻልም ሆነ ለሕብረተሰብ ዕድገት ያለውን አስተዋፅኦ ይገነዘባሉ።
- ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን የዕውቀትና የማስረጃን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የዕውቀትን ትርጉምና አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣ | 11.1 የዕውቀት ምንነትና ጥቅም ፣ (1ክፍለ ጊዜ)<br>11.1.1 የዕውቀት ምንነት፣<br>11.1.2 የዕውቀት ጥቅም፣<br>- ጐበዝ ተማሪና ተመራማሪ ለመሆን፣ | • ተማሪዎች ት/ቤት የሚመጡት ለምን እንደሆነና ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ደግሞ ምን መሆን እንደሚፈልጉ ተራ በተራ እንዲናገሩ ማድረግ። በመረጡት ሙያ ወይም የሥራ ዘርፍ ለመሰማራት ደግሞ ምን እንደሚያስፈልጋቸው እንዲሁ በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ።<br>• በዚህ ጉዳይ የክፍል ውይይቱን በማጠናከር ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ለመሆን ለዚያ ሙያ የሚያበቃቸው ዕውቀትና ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚገባና ይህንንም ለማግኘትከአሁኑ ለትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው በውይይታቸው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ።<br>• የተማሩ ታላላቅ ሰዎችን ታሪክ በሞዴልነት በማቅረብ ለውይይታቸው ማጠናከሪያ እንዲሆን ማድረግ። |
| • የመረጃን ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• መረጃዎች የሚጠኑባቸውን ዘዴዎች ይዘረዝራሉ፣ | 11.2 መረጃ የሚገኝባቸው ዘዴዎች (2ክፍለ ጊዜ)<br>11.2.1 የመረጃ ምንነት፣<br>11.2.2 አካባቢያዊ መረጃዎችን ማመንጨት፣<br>11.2.3 መረጃዎችን ማጣራት<br>11.2.4 መረጃዎችን በዓይነት መከፋፈል፣ | • መረጃ ተጨባጭነት ያለውና ስለአንድ ነገር ዕውቀት የሚሰጠን ነው። በዚህም ዓይነት ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈልና የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት በርዕሶቹ ላይ መረጃ እንዲሰበስቡ ማድረግ። ለምሳሌ በአካባቢያቸው ስለሚበቅሉ አዝርዕት፤ ስለሚከበሩ በዓላት፤ ስለቤተሰባቸው የወር ገቢ፤ በትምህርት ቤታቸው ስላሉ መምህራን ብዛት በፆታ ወዘተ መረጃዎችን እንዲሰበስቡ ማድረግ። እነዚህ ማስረጃዎች ተአማኒነት ያላቸው ስለመሆናቸው ማጣራት።<br>• ለምሳሌ ስለቤተሰባቸው ገቢ አባታቸው ወይም እናታቸው ወይም ተቀባይነት ባለው ጽሑፍ ከሚገኝ መረጃ ይልቅ አጐት ወይም ጐረቤት የሚሰጡት መረጃ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት አይቻልም። በማስከተልም ያገኙዋቸውን መረጃዎች በዓይነት |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | መከፋፈል፣ ለምሳሌ በጽሑፍ የተገኘን ማስረጃ አንድ ላይ፤ ጠይቀው ያገኟቸውን መረጃዎች አንድ ላይ ወዘተ በማደራጀት ተማሪዎች የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ። |
| • ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት በማስረጃ ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸውን በምሳሌ በማስደገፍ ይገልፃሉ፣ | 11.3 ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት፣ (**2ክፍለ ጊዜ**)<br>11.3.1 የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ምንነት፣<br>11.3.2 በማስረጃ ላይ የተመሠረተ አለመሆን፣ | • ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል በአካባቢያቸው የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ውጤቶች ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን አባባሎችን እንዲያሰባስቡ ማድረግ፣ ለምሳሌ «ልጅና ፊት አይበርደውም» «በማዳበሪያ የተዘራ እህል በረከት የለውም» ወዘተ. ተማሪዎች እንደነዚህ ዓይነት አባባሎችን ከሰበሰቡ በኋላ ጥቅም ወይስ ጉዳት እንዳላቸው እንዲገልጹ ማድረግ። በውይይታቸው እነሱ ያሰባሰቧቸው ዓይነት አባባሎች የተሳሳቱ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ውጤት ሊሆኑ የቻሉበት ዋንኛ ምክንያት በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ አለመሆናቸው መሆኑን አጠንክረው እንዲገነዘቡ ማድረግ። ስለሆነም ተማሪዎቹ እነሱ ራሳቸው ስለሚሉት ሆነ ሌሎች ሰዎች ስለሚሏቸው ነገሮች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ማስረጃ አስፈላጊ መሆኑን በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የንባብ ባህል ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• የንባብ ባህልን የማዳበር ጠቀሜ ታን ይገልፃሉ፣<br>• የንባብ ባህላቸውን ለማዳበር ጥረት ያደርጋሉ፣ | 11.4 የንባብ ባህል፣ (**1ክፍለ ጊዜ**)<br>11.4.1 የንባብ ባህል ምንነት፣<br>11.4.2 የንባብ ባህልን ማዳበር ጠቀሜታ፣ | • ትምህርት ቤት ዋናው የዕውቀት ምንጭ ቢሆንም ብቸኛ የዕውቀት ምንጭ ግን አይደለም። ከትምህርት ቤት ውጭ የሰው ልጅ በተለያዩ መንገዶች ዕውቀትን ለማግኘት ይችላል። በመጀመሪያ ተማሪዎች በዚህ ሀሳብ ይስማሙ እንደሆነ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ። በሀሳቡ የሚስማሙ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ደግሞ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ዕውቀት ሊገኙባቸው የሚችሉ ሌሎች መንገዶችን እንዲያብራሩ ማድረግ። ለምሳሌ ከሰዎች ጋር መወያየት፣ ሬዲዮ ማድመጥ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን መከታተል፣ የተግባር ሥራዎችን መሥራት። መጽሐፍት ማንበብ፣ ወዘተ ሊጠቀሱ ይችላሉ፣<br>• በተለይ መጽሐፍትን ማንበብ ከፍተኛ ዕውቀት የሚያስገኝ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ የንባብ ባህላቸውን በማዳበር አንቱ የተባሉ ሰዎችን በመጥቀስ ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውን ማዳበር እንደሚገባቸው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ። |
| • የጥናት ፕሮግራም ያዘጋጃሉ፣<br>• ትምህርቱን ማጥናት ለምን እንደሚጠቅም ይገልፃሉ፣<br>• የትምህርት አጠናን ሥልቶችን | 11.5 የትምህርት አጠናን ዘዴ፣ (**2ክፍለ ጊዜ**)<br>11.5.1 ጥናት ምንድን ነው?<br>11.5.2 ትምህርትን ማጥናት | • ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መምህራን ስለአስተማሯቸው ብቻ በትምህርታቸው ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ትምህርቱን በደንብ ከመከታተል ባሻገር የተማሩትን ትምህርት ማጥናት አለባቸው። ስለዚህ ጥናት የበለጠ ዕውቀት ለማግኘት ስለሚጠቅም ደብተርን፣ መጽሐፍትንና ሌሎች በማጣቀሻነት |

5ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይዘረዝራሉ፣<br>• የትምህርት ጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀት ይጠቀማሉ፣ | ለምን ያስፈልጋል?<br>11.5.3 የክፍል ትምህርትን የማጥናት ስልቶች፣<br>- የጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ | የሚያገለግሉ ነገሮችን በመጠቀም ዕውቀትን ማዳበር አስፈላጊ ነው።<br>• ተማሪዎችን በዚህ ጉዳይ ላይ ማወያየትና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። በተለይ በትምህርት ውጤታማ ለመሆን ዝም ብሎ በዘፈቀደ ማጥናት ሳይሆን በየትኛው ትምህርት ደከም እንደሚሉ በመረዳት የበለጠ ጊዜ መስጠትና ቅደም ተከተል ማበጀት እንደሚያስፈልግ ማወቅ፣ ለጨዋታ ጊዜ መመደብን፣ ቤተሰብን በሥራ ለመርዳት ጊዜ መመደብን፣ ወዘተ መረዳትን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ የጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀትና መጠቀም ተገቢ ይሆናል። በዚህም ጉዳይ ላይ ተማሪዎቹን ማወያየትና የጥናት ፕሮግራም ዝግጅትን እንዲለማመዱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዕውቀትን ትርጉምና አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣የመረጃን ምንነትን ይገልፃሉ፣መረጃዎች የሚጠኑባቸውን ዘዴዎች ይዘረዝራሉ፣ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት በማስረጃ ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸውን በምሳሌ በማስደገፍ ይገልፃሉ፣የንባብ ባህል ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣የንባብ ባህልን የማዳበር ጠቀሜ ታን ይገልፃሉ፣የንባብ ባህላቸውን ለማዳበር ጥረት ያደርጋሉ፣የጥናት ፕሮግራም ያዘጋጃሉ፣ ትምህርቱን ማጥናት ለምን እንደሚጠቅም ይገልፃሉ፣የትምህርት አጠናን ሥልቶችን ይዘረዝራሉ፣የትምህርት ጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀት ይጠቀማሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዕውቀትን ትርጉምና አስፈላጊነት በምሳሌ ያስረዳሉ፣መረጃዎች የሚጠኑባቸውን ዘዴዎች ይዘረዝራሉ፣ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት በማስረጃ ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸውን በምሳሌ በማስደገፍ ያስረዳሉ፣የንባብ ባህልን ያዳብራሉ፣የንባብ ባህልን የማዳበር ጠቀሜ ታን ያስረዳሉ፣የንባብ ባህላቸውን ያዳብራሉ፣የጥናት ፕሮግራም በማውጣት ጥናታቸውን ያከናውናሉ፣ የትምህርት አጠናን ሥልቶችን ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።